የድሕረ ገጻችን ጎብኝዎች
በቅድሚያ እንኳን ደህና መጣችሁ!

ባሁኑ ጊዜ እንኳንስ ድርጅት ግለ-ሰቦችም እንኳን የዕለት ተዕለት ሕይወታቸውን ከሚመሩባቸው የዘመኑ ቴክኒዮሎጂ ግኝቶች አንዱ በኢንተርኔት አማካይነት አገልግሎት ላይ የዋለው ይሕ ድህረ ገጽ የሚባለው ነው።

መኢሶንም እንደማንኛውም ድርጅት ይህንን የቴከኒዎሎጂ መድረክ እስከዛሬ ሳይጠቀምበት መቆየቱ ወዳጆችና ደጋፊዎች ብቻ ሳይሆኑ፤ ማንኛውም ስለድርጅቱ የሚሰማ የሚያነሳው ጥያቄ መሆኑ ግልጽ ነው።

መኢሶን በተለይ ባለፉት 20 ዓመታት ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረገው የነጻነት፤ የፍትህና የዴሞክራሲ ትግል ተሳትፎው፤ ሌሎች ተመሳሳይ አላማ ያላቸውን በማሰባሰብና ከተሰባሰቡም ጋር በመተባበር ለተደረጉ ሥራዎች ቅድሚያን በመስጠት ሲንቀሳቀስ የቆየ ስለነበረና - ይህ ዛሬም የሚቀጥል ነው - ለራሱ ድርጅት የተለየ ትኩረት መስጠቱን ወደሁዋላ በማድረግ ነበር።

ይህ ሲባል ግን፤ በደጋፊዎችም ሆነ በአንዳንድ አባላት በኩል ስለድህረገጽ መከፈት ጉዳይ አልጎተጎቱም ማለት አይደለም። ጉዳዩ ቅድሚያን ከመስጠትና እሱም ከሚጠይቀው ሃይልና አቅም አቅጣጫ በማገናዘም እንጂ፤ የመድረኩን አስፈላጊነትና ጠቃ ሚነት ካለማጤን እንዳልሆነ ግንዛቤ አለ።

ያም ሆነ ይህ፤ ዛሬ ይህንን መድረክ ከፍተናል፤ የመድረኩ አገል ግሎት የምንለውን/የምንላችሁን ብቻ ሳይሆን፤ ጎብኝዎቻችን የምትሉትንም/የምትሉንንም የምናስተናግድበት መድረክ መሆኑን ተገንዝባችሁ የቀድሞ አባላት፤ ወዳጆችና ደጋፊዎች በዚህ ድህረ-ገጽ ሊስተናገዱ ይገባቸዋል የምትሉትን የጽሁፍ አቅርቦታችሁን ላኩልን ለማስተናገድ እንጥራለን።

መልካም ጉብኝት
ከዝግጅት ክፍል